መልእክት ስምንት

## እንደ የእግዚአብሔር ጽኑዕ ኃያል ተዋጊ
## የጌዴዎን ውስጠ-መሠረታዊ አስፈላጊነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ መሣ. 6—9

**I. እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንደ ጽኑዕ ኃያል ተዋጊ አስነሣው እና እስራኤልን ከምድያም ጭቆና (መሣ. 6፡1—8፡32) ለማዳን በእግዚአብሔር ተላከ (መሣ. 6፡12-14፤ ተዛ. ዮሐ. 8፡29)፤ የጌዴዎንን ስኬት ውስጠ-መሠረታዊ አስፈላጊነት ማየት አለብን፦**

ሀ. ጌዴዎን በዚያን ጊዜ በእስራኤል ልጆች መካከል ብርቅ የነበረውን ነገር፣ የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ ሰማ፦

1. በኢኮኖሚው መሠረት ነገሮችን እንመለከት ዘንድ የእርሱን ድምጽ እንድንሰማ ጌታ ሁሌም ጆሮአችንን ሊከፍት ይፈልጋል—ራእ. 1፡10፣ 12፤ ኢዮብ 33፡14-16፤ ኢሳ. 50፡4-5፤ ዘጸ. 21፡6።
2. መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት ሲናገር ሳለ (ራእ. 2፡7) የመንፈስን ንግግር ለመስማት ሁላችንም ክፍት የሆነ፣ የተገረዘ (ኤር. 6፡10፤ ሐዋ. 7፡51)፣ የነጻ (ዘጸ. 29፡20፤ ዘሌ. 8፡23-24፤ 14፡14) እና የተቀባ (ቁ. 17፣ 28) ጆሮ ያስፈልገናል።

ለ. ጌዴዎን የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዘ እና በእርሱም መሠረት አደረገ—ተዛ. ዕብ. 11፡32-33፦

1. በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ የመታዘዝና የመገዛት ሕይወት አለን፣ በመንፈስ የምንመላለስ ከሆንን ቅጽበታዊ በሆነ መንገድ የሕግን የጽድቅ ጥያቄ እናሟላለን—ፊልጵ. 2፡5-11፤ ሮሜ. 8፡4።
2. ወደ ሕጉ ስንመጣ ያለን አመለካከት በፊደል ላሉት ትእዛዛት ግድ መሰኘት ብቻ ከሆነ፣ ሕጉ በሚገድለው ፊደል ገጽታ ይኖረናል፤ ነገር ግን እያንዳንዱን የሕጉን ክፍል በምንወደው አምላክ እንደተተነፈሰ ቃል ከወሰድነው፣ ሕጉ ሕይወትን በሚሰጠው መንፈስ ገጽታ ይኖረናል፤ ከዚያ ሕጉ የእግዚአብሔር አፍቃሪ ፈላጊዎቹ ወደሆንነው ወደ እኛ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለማደል ያገለግላል—መዝ. 119፡25፣ 116፣ 130፤ 2 ቆሮ. 3፡6፤ 2 ጢሞ. 3፡16-17።
3. ሕያውና ንቁ መሆን ማለት ለጌታ መጨመርና መሠራጨት በመንፈስ በውስጥና በውጪ በመሞላት እና ወደ ቃሉ ውስጥ በመግባት በማንኛውም ጊዜ እና በማንኛውም ስፍራ ወንጌልን በመስበክ እና እውነትን በማስተማር ሕያውና ንቁ መሆን ነው—ዳን. 11፡32፤ ሐዋ. 13፡52፤ 4፡8፣ 31፤ 13፡9፤ 2፡38፤ 5፡32፤ 2 ጢሞ. 4፡1-2።

ሐ. ጌዴዎን የበዓልን (የከነዓናዊያን ዋና ተባእት አምላክ) መሠዊያ አፈረሰ፣ ዐፀዱንም (ዋና እንስት አምላክ) ቆረጠ፤ ሚስቱ እስራኤል እንዳመነዘረችባቸው ወንዶች የሚቆጥራቸውን ጣዖታትን እግዚአብሔር ይጠላ ስለነበር ይህ የእግዚአብሔርን ልብ ነካ፤ ውስጣዊ በሆነ መንገድ ከጌታ በላይ የምንወደው እና በሕይወታችን ጌታን የሚተካ በውስጣችን ያለ ማንኛውም ነገር ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ ጣዖት ነው—መሣ. 6፡25-28፤ ሕዝ. 14፡1-3።

መ. የአባቱ የሆነውን የበዓል መሠዊያ በማፍረስና ዐፀዱን በመቁረጡ ጌዴዎን እግዚአብሔርን (ያህዌን) ለመከተል ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት እና የማኅበረሰብ ድሰታውን መሥዋዕት አደረገ፤ ለጌዴዎን እንዲህ ያለውን ነገር ማድረግ የራሱን ፍላጎት መሥዋዕት ማድረግን ጠይቋል፣ መሥዋዕቱ ደግሞ የእርሱ ስኬት ጠንካራ ምክንያት ነበር—መሣ. 6፡28-32።

ሠ. ከላይ በተጠቀሱት አራት ምክንያቶች የተነሣ ጌዴዎን ሽልማትን ተቀበለ—ገቢራዊው መንፈስ በእርሱ ላይ ወረደ (ቁ. 34)፤ ከዚህ የተነሣ ኃይለኛ ሆነ፣ በሦስት መቶ ሰዎችም ብቻ "በብዛት እንደ አንበጣ" እና "ቁጥር እንደሌላቸው ግመሎች" (ቁ. 5፤ 7፡25፤ 8፡10-12) ሰዎች የነበሯቸውን ሁለት መኳንንት እና ሁለት ነገሥታት አሸነፈ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ለመፈጸምና የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ ለማከናወን ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት የኖረ ሰው፣ የአምላክ-ሰው ስዕል በጌዴዎን አለን።

**II. እግዚአብሔር ጌዴዎንን እና ሦስት መቶዎቹ ምድያማውያንን ለማሸነፍ ከእርሱ ጋር ለውጊያ የወጡትን ሰዎች በመምረጡ የድል ነሺዎቹ መመረጥ ይታያል—6፡1-6፣ 11-35፤ 7፡1-8፣ 19-25፤ 8፡1-4፦**

ሀ. የጌዴዎን ታሪክ ድል-ነሺ እንዴት እንደምንሆን ያሳየናል፦

1. ከሁሉ እንደምናንስ በመገንዘብ እኔነትን ማወቅ አለብን—6፡15፤ ኤፌ. 3፡8፤ ማቴ. 20፡27-28፤ ገላ. 6፡3።
2. እንደ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ማዕከላዊነትና አጽናፍ-ዓለማዊነት የክርስቶስን ሰማያዊ ራእይ ማየት አለብን—መሣ. 6፡12፤ ሐዋ. 26፡16-22፤ ቆላ. 1፡17፣ 18፤ 1 ጢሞ. 1፡3-4፤ ፊልጵ. 3፡8፣ 10።
3. የክርስቶስ አካል እውነታና ኑሮ እንዲኖረን በጎ፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም በሆነው ፈቃዱ መሠረት ራሳችንን እንደ ሕያው መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ማቅረብ አለብን (ሮሜ 12፡1-5፤ ተዛ. መሣ. 6፡21-24)፤ በራእይ 2 እና

3 ለድል ነሺዎች ያለውን የጌታን ጥሪ መስማትና ምላሽ መስጠት አለብን—2፡7፣ 11፣ 17፣ 26-28፤ 3፡5፣ 12፣ 20-21፤ ከእንግሊዝኛ የመዝሙር መጽሐፍ ቁጥር 894።

4. በአንድ በኩል እግዚአብሔር ወደ ክርስቶስ እንደ ሕይወት፣ ብርሃንና ኃይል ድሰታ ውስጥ እንደሚመራን እና በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቶስን እንደ እርካታችን እንድንወስደው፣ በክርስቶስ እንድንሞላ እና ክርስቶስ በሁሉ ነገር የመጀመሪያ ስፍራ እንዲኖረው እንፈቅድ ዘንድ የገንዘብ ችግሮች፣ ስሜትን የሚነኩ መከራዎች፣ አካላዊ መከራዎች እና ተፈጥሯዊ መልካምነትን እንድናጣ እግዚአብሔር ሲፈቅድ ታማኝ እንደሆነ በመገንዘብ በልባችን፣ በሕይወታችንና በሥራችን ያሉትን ጣዖታት ለጌታ ምስክር ማፍረስ አለብን—መሣ. 6፡25-28፤ ዮሐ. 10፡10፤ 8፡12፤ 2 ጢሞ. 2፡1፤ ቆላ. 1፡17፣ 18፤ 1 ዮሐ. 5፡21፤ ኢዮ. 22፡24-26፤ ማቴ. 10፡35-39፤ 2 ቆሮ. 12፡7-9፤ ኢዮብ 1፡1፣ 22፤ 2፡9-10፤ 3፡1፣ 11፤ 2 ቆሮ. 4፡5፤ 1 ቆሮ. 2፡2።

ለ. ድል ነሺዎቹ እንዴት እንደሚመረጡ በሦስት መቶዎቹ መመረጥ ታይቷል፤ በጣም ብዙ ሰዎች እንዳሉት ለጌዴዎን በመንገር እግዚአብሔር ለእስራኤል እንደሚዋጋ እያመለከተ ነበር፤ የመጀመሪያው ምርጫ የሃያ ሁለት ሺዎቹ ትቶ መመለስ አስከትሏል፦

1. ትተው የሄዱት ራሳቸውን ማክበር ፈለጉ—መሣ. 7፡1-2፤ ዮሐ. 5፡41፣ 44።
2. ትተው የሄዱት በስጋት የተሞሉና የፈሩ ነበሩ—መሣ. 7፡3፤ ማቴ. 25፡25፤ ተዛ. ዘዳ. 20፡5-8።

ሐ. ሁለተኛው ምርጫ የተወሰነው ሕዝቡ ውኃ በጠጣበት መንገድ ነበር፤ በቀጥታ በአፋቸው ተደቅነው የጠጡት በእግዚአብሔር ተወግደዋል፤ በእጃቸው ወደ አፋቸው ውኃ በማምጣት የጠጡት በእግዚአብሔር ተመርጠዋል ምክንያቱም ራሳቸውን የሚከዱ ሰዎች ነበሩ፤ በዚህ መንገድ በመጠጣት ከጠላት ከሚመጣ ማንኛውም ጥቃት ተግተው በንቃት መጠበቅ ችለው ነበር—መሣ. 7፡4-6፦

1. የራሳቸውን ሥጋዊ ምኞት የማርካት ዕድል ያላቸው ነገር ግን እንደዚያ የማያደርጉት እነርሱ በውጊያው ቀን ስለ እግዚአብሔር አላማ የግል እረፍታቸውንና ምቾታቸውን በመሠዋት በመስቀሉ የታደቡ ራሳቸውን የሚከዱ ሰዎች ናቸው—ቁ. 7፤ መዝ. 110፡3።
2. ድል ነሺዎቹ ለእግዚአብሔር ክብር ፍጹም ናቸው፣ እና ጌታን ከማሳዘንና መገኘቱን ከማጣት ውጭ ምንም ነገር አይፈሩም (ዘጸ. 33፡14-16)፤ መስቀሉ እኔነታቸውን እንዲያስወግድ ይፈቅዳሉ (1 ዮሐ. 3፡8፤ ዕብ. 2፡14፤ ሮሜ 6፡23፤ ገላ. 2፡20)።

መ. እግዚአብሔር ለጌዴዎን ሦስት መቶ ሰዎችን ሰጠው እና ለምድያማውያን ሽንፈትና ለእግዚአብሔር ድል ወደ ምድያም ሰፈር ተንከባልላ በወረደችው በ“አንዲት የገብስ እንጎቻ” እንደተመሰለው አንድ አካል አደረጋቸው—መሣ. 7፡9-25፦

1. በመንፈስ ያለውን አንድነትና በአካሉ ያለውን ኑሮ በማመልከት ጌዴዎንና የእርሱ ሰዎች በአንድነት እንደ አንድ ሰው ተንቀሳቀሱ እና አደረጉ፤ መጀመሪያ በሚደርሰው እህል፣ በገብሱ (መሣ. 6፡16፤ 2 ሳሙ 21፡9፤ ዘሌ. 23፡10፤ 1 ቆሮ 15፡20) እንደተመሰለው ቤተ ክርስቲያንን እንደ ምሳሌ የሚያሳየውን አንድ እንጎቻ ለመሆን (10፡17) በትንሣኤ በአንድነት ተዋሐዱ።
2. ቤተ ክርስቲያን አንድ እንጀራ ስለመሆኗ የጳውሎስ ሃሳብ ከብሉይ ኪዳን የእህል ቁርባን የተወሰደ ነው (ዘሌ. 2፡4-5)፤ የቤተ ክርስቲያንን ቂጣ፣ ኅብስት ለመሥራት (1 ቆሮ. 12፡24-25) በዘይት እንደተለወሰው የላመ ዱቄት እንፈጭ ዘንድ እኛ ብዙ ስንዴዎች ነን (ዮሐ. 12፡24-25)።
3. ተግባራዊ ለሆነው የአካሉ ኑሮ ሁሉንም ነገር በመንፈስ ያደርጉና አንዳቸው ወደሌላቸው ውስጥ ክርስቶስን ያድሉ ዘንድ ማረቅን የተለማመዱ፣ የተዋሐዱ (የተገጣጠሙ) እና የተሰቀሉ ለመሆን እየተማሩ ላሉት ሞዴል፣ የአካሉ ሕይወት ሞዴል ይሆኑ ዘንድ ሁሉም አብሮ-ሠራተኞችና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እርስ በእርስ በእረኝነት መንከባከብና እርስ በእርስ መዋደድ አለባቸው—ሮሜ 12፡1-5፤ ተዛ. 2 ዜና 1፡10።

ሠ. እኛ ድል ስንነሣ፣ ያሕዌ እንደ ሰላም፣ ያሕዌ-ሻሎም (መሣ. 6፡24)፣ በምድር እስኪነግሥ ድረስ የመላ አካሉ መነቃቃትን በማመልከት ጌዴዎንና ሦስት መቶዎቹ ሰዎች ውጊያውን ተዋጉ እና ተጉ፣ ነገር ግን መላው ማሕበር ጠላትን አሳደደ፣ መከሩንም አጨደ—7፡22-25፤ 8፡1-4፤ ቆላ. 1፡24፤ መዝ. 128፡5፤ ኢሳ. 32፡17፤ 66፡12።

ረ. ጌዴዎንና የእርሱ ሰዎች የምድያምን ነገሥታት ሲያሳድዱዱ ሳሉ “ምንም እንኳን ቢደክሙ ያሳድዱ ነበር” (መሣ. 8፡4)፤ ለማገልገል የእግዚአብሔርን ምሕረት ስለተቀበልን እና በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ እውነታ ውስጥ ስለምንኖር አንታክትም (2 ቆሮ. 4፡1፣ 16-18)፤ እስከ መጨረሻ ነጥብ ድረስ ልንተጋ እንችላለን፣ ነገር ግን ትጋታችን በእኛ ውስጥ በኃይል በሚሠራ በእግዚአብሔር አሠራር መሠረት ነው (ቆላ. 1፡28-29፤ 1 ቆሮ. 15፡58)።

## III. የጌዴዎንን ውድቀት ምስጢር ውስጠ-መሠረታዊ ትርጉም ማየት አለብን፦

ሀ. በመጀመሪያ፣ ጌዴዎን ቸር አልነበረም፤ ስድስተኛውን የእግዚእሔርን ትእዛዝ በመጣስ (ዘጸ. 20፡13) እርሱን ያልደገፉትን ሽማግሌዎች ገደለ (መሣ. 8፡16-17)፤ ክርስቶስ እንደ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ መራን (ሮሜ 2፡4፤ ቲቶ 3፡4፤ ኤፌ. 2፡7)።

ለ. ሁለተኛ፣ በሥጋዊ ምኞቱ ላይ ምንም አይነት መገደብ ሳያደርግ ሥጋዊ ምኞቱን ፈጸመ (ተዛ. ገላ. 5፡16፤ ሮሜ 8፡4)፤ ይህ "ብዙ ሚስቶች ነበሩትና" በሚለው እና ጌዴዎን ሰባ ልጆች እንደ ነበሩት በሚነግረን በመሣፍንት 8፡30 ታይቷል፤ በተጨማሪም በሴኬም የነበረችው ቁባቱ ወንድ ልጅ ወለደችለት (ቁ. 31)፤ በዚህ ጌዴዎን ሰባተኛውን ትእዛዝ አፈረሰ (ዘጸ. 20፡14)።

ሐ. ሦስተኛ፣ ሕዝቡ ላይ መግዛትን እምቢ በማለቱ መልካም ነገር ቢያደርግም (መሣ. 8፡22-23)፣ አሥረኛውን ትእዛዝ በማፍረስ የሕዝቡን ምርኮ (የወርቅ ጉትቻ) ተመኘ፣ እነርሱም እሺ ብለው ሰጡት፤ ጌዴዎን ከሕዝቡ በወሰደው ወርቅ ኤፉድ ሠራ፣ ይህ ኤፉድ ደግሞ ለእስራኤል ልጆች ጣዖት ሆነ (ቁ. 24-27፤ ዘጸ. 32፡1-4 እና በቁ. 2 ሥር የግርጌ ማስታወሻ 1)፤ በዚህም ምክንያት የጌዴዎን ቤተሰብና መላው የእስራኤል ሕዝብ ተበላሸ።

መ. መሣፍንት የክርስቶስ ምሳሌ ስለሆነው ስለመልካሚቱ ምድር ድሰታ የሚያወራ መጽሐፍ ነው፤ የጌዴዎን ስኬት ክርስቶስን ለመደሰት ምርጥ እድል ማትረፍን ያሳያል፣ ውድቀቱ ግን ክርስቶስን የመደሰት ዕድል ማጣትን ያሳያል።

IV. **የጌዴዎን ሥጋዊ ምኞቱን መፈጸሙና ለወርቅ የነበረው ስግብግብነት ወደ ጣዖት አምልኮን አመጣ፤ ስግብግብነት ጣዖትን ማምለክ ነው (ቆላ. 3፡5)፣ እና ዝሙትና ስግብግብነት ከጣዖት አምልኮ ጋር የተገናኙ ናቸው(ኤፌ. 5፡5)፤ የእርሱ ውድቀት የወሲብና የሃብትን ጉዳይ በተመለከተ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለብን ያሳየናል፡-**

ሀ. በእስራኤል መንግሥት በዚያ መንግሥት ግርማ ከፍተኛ ጫፍ ላይ የከበረውና (1 ነገ. 4፡34፤ 8፡10-11) እግዚአብሔርን እንደሚፈራና እግዚአብሔርን እንደሚወድ ሰው የጀመረው ንጉሡ ሰሎሞን እንኳን ሳይቀር በብዙ እንግዳ ሚስቶቹ በኩል ጣዖት አምላኪ ሆነ (11፡1-13፤ ቁ. 43 ላይ ያለው የግርጌ ማስታወሻ)።

ለ. ጌዴዎን ከሞተ በኋላ የእስራኤል ዝቅጠት የጀመረው ያሕዌ አምላካቸውን በመተዋቸውና የከነዓናውያንን ጣዖታት በማምለካቸው ነው፣ ይህም ሥጋዊ ምኞታቸውን መፈጸማቸውን አመጣ፤ እንዲሁም የጌዴዎን ቁባት ልጅ አቤሜሌክ የጌዴዎንን ሌሎች ሰባ ልጆች አረደ፣ ሌላኛው ልጅ ኢዮአታም ግን አመለጠ—መሣ. 8፡33-9፡57።

ሐ. ከንቱ ክብርን እምቢ ብለው ለእግዚአብሔር ሕዝብ የአቅርቦት መንገድ ከሆኑት እንደ የወይራ ዛፍ፣ የበለስ ዛፍ፣ የወይን ዛፍ ከሆኑት በተጻራሪ፣ የአቤሜሌክን ንግሥና እንደ የእሾህ ዛፍ መንገሥ እንደሆነ ኢዮአታም በድፍረት አወጀ (ቁ. 8-13)፤ ሰባ ወንድሞቹን በማረድ አባቱ ላይ ያደረገውን የአቤሜሌክን ክፋት እግዚአብሔር መለሰ (ቁ. 14-55)፤ እና የሴኬም ሰዎችን ክፋት ሁሉ እግዚአብሔር በራሳቸው ላይ መለሰባቸው፣ የይሩበኣልም (ጌዴዎን—6፡32) ልጅ የኢዮአታም እርግማንም ደረሰባቸው (9፡56-57)።

መ. ጌዴዎን በስኬቱ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አጋጠመ፣ በውድቀቱ ግን ራሱን ከሰይጣን ጋር አጋጠመ፤ እግዚአብሔርን መተውና ከሰይጣን ጋር መተባበር በዚህ በክፉው ውስጥ ወዳለ ውስጣዊ ምኞት ውስጥ መግባት ነው—ኢሳ. 14፡13-14።

ሠ. ጌታን ለመፍታት ምንም መብት የለንም፣ እርሱንም ለመተው ምንም ምክንያት የለንም፤ ሰይጣንን እስከመጨረሻ በመቃወም ጌታን መውሰድ፣ እርሱን ማፍቀር፣ እርሱን ማክበር፣ እርሱን መመልከት፣ እርሱን ከፍ ማድረግ እና ከእርሱ ጋር መጣበቅ አለብን፤ ከዚያ የተባረክን እንሆናለን፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ጌታ፣ ራስ፣ ንጉሥ እና ባል የሆነለት ሁሉ—አገር፣ ማህበረሰብ፣ ቡድን፣ ግለሰብ—የተባረከ ነው—መዝ. 33፡12።

*© 2021 Living Stream Ministry*